# JKF ፖሊሲ- የአካል ጉዳት ባለባቸው ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ

I. የአካል ጉዳት ባለባቸው ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ

A. በዚህ ፖሊሲ እና በፌደራል እና በስቴት ሕጎች በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በቀር፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች በስኩል ዲስትሪክቱ የተማሪ ስነምግባር እና ዲስፕሊን ደንብ እና ፖሊሲዎች እንዲሁም የተማሪዎችን ዲሲፕሊን በሚገዙ አሰራሮች በሙሉ ተገዢ ይሆናሉ። የትምህርት ቤት ሠራተኛ አሁን ባለበት ወይም ባለችበት የትምህርት ቦታ ላይ ለተማሪ የተቀመጠውን የስነምግባር ደንብ የጣሰ/ች የአካል ጉዳት ያለበት/ባት ተማሪን ካለበት/ችበት ቦታ አስነስቶ ወደ ሌላ አማራጭ የመማሪያ ቦታ ሊወስደው/ዳት ወይም ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ከትምህርት ገበታው/ዋ ሊያግደው/ዳት፣ ከትምህርት ገበታው/ዋ መነሳቱ/ዋ የተመደበበትን/ችበትን ቦታ ለውጥ የማያመጣ ከሆነ በአንድ ተመሳሳይ የትምህርት ክፍለ ዘመን ለተፈጠሩ የተለያዩ የስነምግባር ጉድለቶች ለተጨማሪ ከ 10 ተከታታይ ቀናት ያልበለጡ የትምህርት ቀናት ሊያግደው/ዳት ይችላል።

II. መግለጫዎች

A. የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ማለት በአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የትምህርት ማሻሻያ ሕግ (Individuals with Disabilities Education Improvement Act /IDEA '04) ወይም በ1973ቱ የመልሶ ማቋቋሚያ ሕግ (Rehabilitation Act of 1973) ክፍል 504፣ በተሻሻለው (ክፍል 504)፣ ወይም በስኩል ዲስትሪክቱ አሰራር መሰረት የአካል ጉዳት እንዳለባቸው ተለይተው የታወቁ ተማሪዎችን ያጠቃልላል። የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ሃሳብ እንዲቀርብ ያስቻለውን ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት አንድ ተማሪ በሚከተሉት ሁኔታዎች በ IDEA '04 የተቀመጡ የአካል ጉዳተኝነት ጥበቃዎች እንዲደረጉሉት መጠየቅ ይችላል፥

1. የተማሪው ወላጅ ለትምህርት ቤቱ ተቆጣጣሪ (ሱፐርቫይዘር) ወይም ለስኩል ዲስትሪክቱ የአስተዳደር ሠራተኛ ወይም የተማሪው መምህር በጽሑፍ ልጁ የልዩ ትምህርት አገልግሎት እንደሚያስፈልገው የጠየቀ እንደሆነ፣ ወይም

2. የተማሪው ወላጅ ተማሪው ልዩ የትምህርት አገልግሎት ለማግኘት ተገቢነት እንዳለው ለማወቅ አስፈላጊው ፈተና እንዲሰጠው ከጠየቀ፣ ወይም

3. የተማሪው አስተማሪ ወይም ሌላ የስኩል ዲስትሪክቱ ሠራተኛ በግልጽ ተማሪው በልዩ ትምህርት መስተናገድ እንዳለበት የሚጠቁሙ ባሕሪዎችን ስለማሳየቱ ለልዩ ትምህርት ዳይሬክተሩ ወይም (በስኩል ዲስትሪክቱ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልገውን ተማሪ ለይቶ ማወቂያ እና ወደሚመለከተው አካል አላላክ መሰረት) ለሚመለከታቸው ሌሎች ተቆጣጣሪ ኃላፊዎች ካሳወቀ።

በልዩ ሁኔታ የሚታለፉ ነገሮች፥ ተማሪው በዚህ ፖሊስ መሰረት ጥበቃ እንዲያገኝ ሊያረጋግጥ ሳይችል ሲቀር።

1. ተማሪው ምርመራ ተደርጎለት የአካል ጉዳት እንደሌለበት ከተረጋገጠ፣ ወይም ምርመራ ማድረጉ አስፈላጊ እንደሆነ ካልታመነበት፣ እና የተማሪው ወላጅ(ጆች) ስለ ተገቢነቱ ወይም ምርመራ ማድረግ ስላለማስፈለጉ ውሳኔ ላይ ስለመደረሱ እንዲያውቁት ከተደረገ።

2. ወላጅ ተማሪው ልዩ ትምህርት እንዲሰጠው ምርመራ እንዲደረግለት ካልፈቀደ።

3. ተማሪው ልዩ ትምህርት እንደሚያስፈለገው ታምኖበት ሳለ፣ ወላጅ ግን አገልግሎቱ እንዳይሰጠው ከተቃወመ።

B. መታገድ። ለዚህ ፖሊስ ተፈጻሚነት፣ መታገድ ማለት ከአስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቤት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ከትምህርት ቤት ለአንድ ጊዜ መወገድ ማለት ነው። እገዳዎች ተማሪው በአንድ የትምህርት ቀን ከሚማረው የትምህርት መርሃ ግብር ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ለተወሰነ ጊዜ መወገድን ያጠቃልላሉ።

C. በት/ቤት ውስጥ መታገድ። ለዚህ ፖሊሲ ተፈጻሚነት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረግ መታገድ እንደ ተወሰደ ዲሲፕሊን እርምጃ መመዝገብ ያለባቸው ሲሆን፣ ነገር ግን ተማሪው በመደበኛው አጠቃላይ የትምህርት መርሃ ግብር ልዩ ትምህርት አገልግሎት ማግኘቱን ለመቀጠል ዕድል የሚያገኝበት ሁኔታ እስካለ ድረስ እና የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር አሁን ባለው ምደባ እኩል ተሳትፎ ማድረግ እስከቻለ ድረስ፣ ተማሪው በአጠቃላዩ የአጭር ጊዜ መወገድ ጋር እኩል 10 የተጠራቀሙ መታገዶችን ሊስተካከል በሚችል ሁኔታ አጫጭር በት/ቤት ውስጥ መታገዶች ሊመዘገቡበት አይገባም።

D. መባረር፥ ለዚህ ፖሊሲ ተፈጻሚነት፣ መባረር ማለት በተማሪው የአካል ጉዳት የተነሳ የተንጸባረቀ የስነምግባር ጉድለት እንዳልሆነ ከተረጋገጠ እና ለአንድ ተማሪ ያልተገባ ጠባይ ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ከትምህርት መርሃ ግብር መታገድን ጨምሮ በስቴት ሕግ መሰረት የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ ማለት ነው።

E. የምድብ ቦታ ለውጥ፥ ለዚህ ፖሊሲ ተፈጻሚነት፣ የምድብ ቦታ ለውጥ ማለት ተማሪው በሚከተሉት ሁኔታዎች አሁን ካለበት መማሪያ ቦታ እንዲወገድ ሲደረግ ማለት ነው፥

1. ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ መወገድ፣ ወይም

2. በተደጋጋሚ ከትምህርት ገበታ በመታገድ የድግምግሞሽ ባሕሪ ከተፈጠረ። የድግምግሞሽ ባሕሪ መፈጠሩን ለማወቅ የሚከተሉት መስፈርቶች ከግምት ይገባሉ፥

i. በአንድ የትምህርት ክፍለ ዘመን ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ከትምህርት ገበታ መታገድ፣

ii. ተማሪው እንዲወገድ በተደረገባቸው ጊዜያት ሁሉ የመወገዱ ምክንያት ተመሳሳይ ሆኖ ሲገኝ፣ እና

iii. የእያንዳንዱ መወገድ ርዝመት፣ ተማሪው ተወግዶ የቆየበት ጊዜ ርዝመት እና ከአንዱ መወገድ እና ከሌላው መወገድ መካከል ያለው የጊዜ ቅርበት።

3. የድግምግሞሽ ባሕሪ የምድብ ቦታ ለውጥን ማስከተል ስለመቻሉ ለመወሰን ዲስትሪክቱ እያንዳንዱ የሚቀርብለትን ጉዳይ አንድ በአንድ ይመረምራል።

F. ጊዜያዊ አማራጭ የመማሪያ ቦታ (Interim Alternative Educational Setting /IAES): ያልተፈለገው ባሕሪ የተፈጠረው በተማሪው የአካል ጉዳተኝነት የተነሳ መሆን አለመሆኑ ከግምት ሳይገባ በሚከተሉት ሁኔታዎች አንድ ተማሪ ከትምህርት ገበታው ተወግዶ ወደ IAES ለ45 ቀናት እንዲሄድ በ IEP ቡድን ሊወሰን ይችላል፥

a) በት/ቤት ውስጥ፣ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ትምህርት ቤቱ በሕግ ወይም ለት/ቤቱ በስቴት የትምህርት ኤጀንሲ በተፈቀደለት ክልል ውስጥ የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት፣

b) በት/ቤት ውስጥ፣ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ትምህርት ቤቱ በሕግ ወይም ለት/ቤቱ በስቴት የትምህርት ኤጀንሲ በተፈቀደለት ክልል ውስጥ ሆን ብሎ በማወቅ ሕገ ወጥ አደንዛዥ ዕፆችን ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም ወይም የአንድ ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገርን ሽያጭ መፈጸም ወይም ማሻሻጥ፣ ወይም

c) በት/ቤት ውስጥ፣ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ትምህርት ቤቱ በሕግ ወይም ለት/ቤቱ በስቴት የትምህርት ኤጀንሲ በተፈቀደለት ክልል ውስጥ በሌላ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ። ከባድ የአካል ጉዳት ማለት ሞት ሊያስከትል የሚችል፣ ከባድ የአካል ሕመም፣ ለተራዘመ ጊዜ የሚቆይ ወይም በግልጽ የሚታይ የአካል/ የፊት መበላሸት፣ ወይም የአንድ የሰውነት ክፍል፣ ብልት ወይም የአእምሮ ክፍል ለተራዘመ ጊዜ ከአገልግሎት ውጭ መሆን ወይም ለዘለቄታው የመስናከል ጉዳት ማለት ነው።

III. እገዳዎች

A. በአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ላይ የሚጣል እገዳ እንደ አካል ጉዳት የሌለባቸው ተማሪዎች ሁሉ ከ 10 ተከታታይ ቀናት ባልበለጠ ሁኔታ ሊፈጸም ይችላል።

B. አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት ክፍለ ዘመን ከአንድ በበለጠ የስነምግባር ጉድለት ሊታገድ የሚችል ቢሆንም እያንዳንዱ እገዳ ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት መብለጥ እና የድግምግሞሽ ባሕሪን የያዘ መሆን የለበትም። የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ከተማሪው የልዩ ትምህርት አስፈጻሚ ባለሙያ ጋር በመተባበር የምደባ ቦታ ለውጥ መደረግ አለመደረጉን ይወስናሉ።

C. የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም ለተለየ የስነምግባር ጉድለት በተደረጉ መወገዶች የተነሳ የሚፈጠር የምደባ ቦታ ለውጥ የባሕሪ መገለጽ መወሰኛ ግምገማ እንዲደረግ ምክንያት ይሆናል። በተጨማሪ፣ ወላጆች ስለሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ እና አሰራሩ ይዘት እንዲያውቁት ይደረጋል።

D. አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ በአንድ ተመሳሳይ የትምህርት ክፍለ ዘመን አሁን ካለበት/ችበት ምድብ ቦታ ለ 10 የትምህርት ቀናት የተወገደ/ች ከሆነ/ች፣ በመደበኛው አጠቃላይ የትምህርት መርሃግብር መሳተፉ/ፏን መቀጠል እንዲችል/እንድትችል፣ የት/ቤቱ ሠራተኛ ከተማሪው/ዋ የልዩ ትምህርት አስፈጻሚ ባለሙያ ጋር በመመካከር፣ ምን ዓይነት አገልግሎት ተማሪው/ዋ እንደሚያስፈልገው/ጋት የሚወስን ቢሆንም በሌላ ሁኔታ ደግሞ፣ በተማሪው/ዋ IEP ላይ የተቀመጡ ግቦችን ለመምታት መፍትሔ ሊያፈላልጉ ይችላሉ።

IV. መባረሮች

A. አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ከት/ቤት መባረር ካለበት፥

1. ይህን የአሰራር እርምጃ ተገቢነት ባለው ሕግ ተደግፎ ውሳኔው በተሰጠበት ቀን ለተማሪው ወላጆች ውሳኔውን እንዲያውቁት ይደረጋል፣ እና

2. ይህ ካልሆነ በተቻለ ፍጥነት ውሳኔው በተሰጠና ተማሪው በታገደ በአስር (10) ቀናት ውስጥ መሆን ሲኖርበት፣ የ IEP ቡድን እና ሌሎች የሙያ ብቃት ያላቸው የዲስትሪክቱ ሠራተኞች  በተማሪው አካል ጉዳተኝነት

እና በስነምግባሩ መካከል ያለውን ዝምድና እና ግንኙነት ለማወቅ የባሕሪ መገለጽ መወሰኛ ግምገማ ማድረግ አለባቸው።

V. የባሕሪ መገለጽ መወሰኛ ግምገማ

A. በባሕሪ መገለጽ መወሰኛ ግምገማ ወቅት፣ ርዕሰ መምህሩ/ወኪሉ፣ ወላጅ(ጆች) እና ተገቢነት ያላቸው የ IEP ቡድን አባላት (ማንነታቸው በወላጅ እና ብዲስትሪክቱ የሚወሰን ሆኖ) የሚከተሉትን ይገመግማሉ፥

a) ሁሉም በተማሪው ማህደር ውስጥ ያሉ ተዛማጅነት ያላቸው መረጃዎች።

b) የተማሪው IEP፣

c) የመምህሩ ግምገማ፣ እና

d) ማናቸውም በወላጅ(ጆች) የተሰጠ ማናቸውም ተዛማጅ መረጃ።

ቡድኑ የሚከተለውን ይወስናል፥

1. የስነምግባር ችግሩ የተከሰተው ትምህርት ቤቱ የሚያስፈልገውን የልዩ ትምህርት አገልግሎት፣ ደጋፊ አጋዥ መሳሪያዎች እና አገልግሎቶች፣ የባሕሪ ማስታረቂያ መርሃግብሮች እና/ወይም በተማሪው IEP ለተማሪው ያስፈልገዋል ተብሎ የተመደበበትን ምድብ ቦታ ባለመስጠቱ የተከሰተ ችግር መሆኑ አለመሆኑን፣ ወይም

2. የስነምግባር ችግሩ በቀጥታ ከአካል ጉዳተኝነት ችግሩ ጋር በተያያዘ የተፈጠረ ችግር መሆኑን።

የ IEP ቡድን ከላይ በቁጥር 1 እና 2 የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች እንዳልተሟሉ ከወሰነ የስነ ምግባር ችግሩ የተማሪው የአካል ጉዳተኝነት ያስከተለው የባሕሪ መገለጫ አይደለም ማለት ነው። የስነምግባር ጉድለቱ የተፈጠረው ከተማሪው የአካል ጉዳተኝነት ያስከተለው የባሕሪ መገለጫ ምክንያት እንዳልሆነ ከተወሰነ፣ የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ለሌሎች የአካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ተማሪዎች የተቀመጡትን የስነምግባር እርምጃዎች በተመሳሳይ መልኩ እና የጊዜ ርዝማኔ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ሆኖም ግን፣ ተማሪው በመደበኛው አጠቃላይ የትምህርት መርሃግብር መሳተፍ እንዲችል ምንም እንኳን በሌላ ሁኔታዎች የተማሪው IEP ግብ እንዲመታ የተቀመጡ ስልቶች በ IEP ቡድኑ በሌላ መልኩ የተገለጹ ሊሆኑ ቢችሉም ተማሪው የትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘቱን ይቀጥላል።

የ IEP ቡድን ከላይ በቁጥር 1 እና 2 የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች አንዳቸው የተሟሉ መሆናቸውን ከወሰነ የስነ ምግባር ችግሩ የተማሪው የአካል ጉዳተኝነት ያስከተለው የባሕሪ መገለጫ ነው ማለት ነው። የ IEP ቡድኑ በዚህ ክፍል ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተቀመጠው መስፈርት እንደተሟላ ከወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ አለበት። የትምህርት ቤቱን የስነምግባር ደንብ እንዲጣስ ምክንያት የሆነው ነገር የተማሪው የአካል ጉዳተኝነት ችግር መሆኑ ከተወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ የሚከተሉት ነገሮች ካላገዱት በቀር ተማሪውን ወደ ምድብ ቦታው መመለስ አለበት፥

a. ወላጅ/አሳዳጊ እና ዲስትሪክት በተደረገው የምደባ ቦታ ለውጥ ተስማምተዋል፣ ወይም

b. ዲስትሪክቱ የምድብ ቦታ ለውጥ በሕግ የተቀመጠ ሆኖ ሲያገኘው፣ ወይም

c. ተማሪው በጊዜያዊ አማራጭ መማሪያ ቦታ ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት የተመደበ ከሆነ።

ተማሪው ያሳየውን የባሕሪ ጉድለት ለማረቅ እና ሁለተኛ እንዳይፈጠሩ ለማድረግ ሲባል ተማሪው እንደ አስፈላጊነቱና ተገቢነቱ ተግባራዊ የባሕሪ ማስተካከያ፣ ግምገማ ኣና ማስታረቂያ አገልግሎቶች ሊሰጡት ይገባል። ተግባራዊ የባሕሪ ማስተካከያ ግምገማ ተደርጎ የተጠናቀቀ እና የስነምግባር ጉድለቱ ከመፈጸሙ በፊት የባሕሪ ማስታረቂያ ዕቅዱ ተዘጋጅቶ የነበረ ከሆነ፣ በጥያቄ ላይ ያለውን የስነምግባር ጉድለት ለማረቅ እንደአስፈላጊነቱ እንደገና ይታያል እና ይሻሻላል።

VI. ጊዜያዊ አማራጭ የመማሪያ ቦታ

በዚህ ፖሊሲ ክፍል I (F) በተዘረዘሩን ከተማሪ የአካል ጉዳተኝነት በመነሳት የሚፈጠሩ የስነምግባር ጉድለቶች መሆን አለመሆናቸው ከግምት ሳይገባ የትምህርት ቤት ሠራተኛ አንድን ተማሪ ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የመማሪያ ቦታ ከ 45 የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲሄድ ሊያደርገው ይቻላል። የ IEP ቡድን በመደበኛው አጠቃላይ የትምህርት መርሃግብር መሳተፉ/ፏን መቀጠል እንዲችል/እንድትችል፣ በተማሪው IEP ላይ የተቀመጡ ግቦችን ለመምታት መፍትሔው ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሆነ ይወስናል።

VII. በክፍል 504 መሰረት እንደ አካል ጉዳተኛ የተፈረጁ ተማሪዎች

በ IDEA '04 ለተቀመጠው "የአካል ጉዳተኛ ተማሪነት" ብቁ ያልሆኑ ነገር ግን በክፍል 504 በተቀመጡ መስፈርቶች ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ላይ የሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል። የክፍል 504 ቡድን፣ የስነምግባር ጉድለቱ የተፈጠረው ከተማሪው የአካል ጉዳተኝነት ያስከተለው የባሕሪ መገለጫ ምክንያት እንዳልሆነ ከተወሰነ፣ የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ለሌሎች የአካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ተማሪዎች የተቀመጡትን የስነምግባር እርምጃዎች፣ እገዳና መባረርን ጨምሮ በተመሳሳይ መልኩ እና የጊዜ ርዝማኔ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። በተጨማሪ፣ የትምህርት መርሃ ግብሩ በክፍል 504 መጽደቅ የማያስፈልገው እና ለአካል ጉዳት የሌለባቸው ተማሪዎች የሚሰጥ የትምህርት መርሃ ግብር እስከሆነ ጊዜ ድረስ መስጠቱን ይቀጥላል።
እንዲጣጣም ተደረጎ የተዘጋጀው፥ ጁን 16፣ 2000

የተሻሻለው፥ ኦገስት 21፣ 2008

ሕጋዊ ዋቢዎች፥

C.R.S. 22-33-106(1)(c)

C.R.S 22-20-10 1 et seq. (Exceptional Children's Education Act)

20 U.S.C. 1401 et seq. (Individuals with Disabilities Education Improvement Act of 2004)

ተዛማጅ ዋቢዎች፥

JK Student Discipline

JK-R Student Conduct and Discipline Procedures